www.abyssinialaw.com

# የተሻሻለው የአፋር ክልል ሕገ መንግስት

# (1994)

www.abyssinialaw.com

አዋጅ ቁጥር__________

# የ1994 ዓመተ ምህረት የተሻሻለው የአፋር ክልል ህገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ

በክልሉ ነዋሪ ሕዝብ ተወካዮች ተመክሮበት የካቲት 9/90 በመጀመሪያ የፀደቀውን እና እስከአሁን ሲሰራበት የቆየውን የክልሉን ህገ መንግሥት በጥልቀት ተመልክቶ በተለይም የክልሉን መንግሥት አካላት የሥልጣን ክፍፍልና ተጠያቂነት በግልፅ መደንገግና ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት መስጠት በሚቻልበት ሁኔታ ህገመንግሥቱን ማሻሻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ።
በሥራ ላይ ባለው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 99 መሠረት ከዚህ የሚከተለው የተሻሻለው የ1994 ዓመተ ምህረት የአፋር ክልል ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ታውጇል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የተሻሻለው የ1994 ዓመተ ምህረት የአፋር ክልል ህገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ________ 1994 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. የተሻሻለው የ1994 ህገ መንግሥት ስለመፅደቁ

በአዋጅ ቁጥር 1/1990 ዓመተ ምህረት የፀደቀው የክልሉ ህገ መንግሥት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ ከታየ በኋላ የተሻሻለው የ1994 ዓመተ ምህረት የአፋር ክልል ሕገ መንግሥት በዚህ አወጅ ፀድቋል።

## 3. ስለነባር ሕጐች ተፈፃሚነት

በሥራ ላይ ያለ ማንኛውም ነባር ሕግ ከተሻሻለው ሕገ መንግሥት ጋር ከተቃረነ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## 4. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከቀን ______ /1994 ዓመተ ምህረት ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ___ 1994 ዓመተ ምህረት
እስማዒል ዓሊሲሮ
የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ
መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር

www.abyssinialaw.com

## 2. መ ግ ቢ ያ

እኛ የአፋር ሕዝብ ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየው አፋኝ ስርዓት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችን ቃፍነው በተዛቡ ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፓሊሲዎች ለድህነትና ኃላቀርነት አጋልጦን መቆየቱ፡ በአጠቃላይ ዕድገታችን ያደረሰው አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ በመፈለግ፤

የአፋር ሕዝብ ያለፉት የኢትዮጵያ ጨቋኝ ሥርዐቶችን ለመደምሰስ ወደር የሌለው መስዋእትነት ከከፈለበት ምክንያቶች አንዱና ዋናው ሁሉም ሰብአዊና ደሞክራሲያዊ መብቶቻቸው የተከበሩ፤ ሕዝቦች በህገ መግሥስትና በሱ ብቻ የምትመራ ዴሞክራሲያዊት ሀገር እንድትሆን በማለት በአብዛኛው የሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ሕዝቦች ላይ ይፈፀም በነበረው አንገፍጋፊ ጭቆና ተጎጂ ሆነን መቆየታችን በማያዳግም ሁኔታ መታረም እንዳለበት በማመን።

መላ የሀገራችን ብሄር፣ ብሄረሰቦች፣ ሕዝቦች ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ አድሃሪውና አፋኙ ስርዓት በሚያስተማምን ሁኔታ ተደምስሶ ኢትዩጵያ ሀገራችን የግለሰብ መብቶችና የብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል የተከበሩበት አጠቃላይ የህግ የበላይነት የነገሰበት ፌደራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መሆንዋ የጋራ ዕድገትን ለማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማሕበረሰብ ማነፅ ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ።

እኛ የአፋር ሕዝብ ለፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለዘላቂ ሰላም ጠንካራ ዲሞክራሲ የምንበቃ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት መሰረት ያደረገና ከብሔራዊ ክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ህግ የተዛመደና የዚህ ክልል ሕዝቦች የተከበሩበትና ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችለን የራሳችን ህገ መንግሥት ሲኖረን መሆኑን በሚገባ በማመን።

በሥራ ላይ ያለው ህገ መንግሥት ከክልሉ ነባራዊ የዕድገት ደረጃና የህብረተሰብ አኗኗር ጋር የተዛመደና ግልፅ አሰራርን የሚከተል በመረጠው ሕዝብ ተጠያቂ የሚሆንና ብቃት ያለው መንግሥታዊ አደረጃጀትን በሚያሳይ አግባብ ጥልቅ መሰተካከል ተደርጎበትና የምንገኝበት ሁኔታ በሚጠይቀው መጠን እንደገና ተሻሽሎ መውጣት ያለበት መሆኑን በውል በመረዳት እነሆ ዛሬ ________________ በሠመራ ከተማ ባካሄድነው የክልል ምክር ቤት ጉባኤ ለዚሁ ዓላማ በተሰየመ አካል ተረቅቆ በቀረበው የተሻሻለዉ ህገ መንግሥት ላይ መክረንና በዝርዝር ተወያይተን ሰነዱን በሙሉ ድምፅ አፅድቀነዋል።

www.abyssinialaw.com

# ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ 1
### የክልሉ መንግሥት ሥያሜ

ይህ ህገ መንግሥት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ አወቃቀርን ይደነግጋል። በዚሁ መሠረት የተቋቋመው መንግሥት "የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት" በሚል ስም ይጠራል።

### አንቀፅ 2
### የአፋር ብሄራዊ ክልል ወሰን

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት መሠረት የቆመ ሆኖ፡፡

በሰሜን ምስራቅ = ኤርትራ

በሰሜን ምዕራብ = ትግራይ ክልል

በደቡብ = ኦሮሚያ ክልል

በደቡብ ምዕራብ = አማራ ክልል

በደቡብ ምስራቅ = ሱማሌ ክልል

በምስራቅ = ጂቡቲ ሪፐብሊክ

የሚያዋስኑት መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ያለው ብሔራዊ ክልል ነው።

### አንቀፅ 3
### ሰንደቅ ዓላማና አርማ

የአፋር ብሔራዊ ክልል የራሱ ሰንደቅ አላማና አርማ ይኖረዋል ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 4
## የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር

የአፋር ብሔራዊ ክልል መዝሙር የሕገ መንግስቱን ዓላማዎች፣ የሕዝቡን የጀግንነት ታሪኩን የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር የዲሞክራሲ ስርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲሁም የክልሉ ሕዝብ ባህል ዕድገትና ብሩህ ተስፋ የሚያንፀባርቅ ሆኖ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 5
## የሥራ ቋንቋ

የክልሉ ብሔራዊ መንግሥት የሥራ ቋንቋ አፋርኛ ነው።

## አንቀፅ 6
## ርዕሰ ከተማ

የክልሉ ርዕሰ ከተማ ሠመራ ነው።

## አንቀፅ 7
## የፆታ አገላለፅ

በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ ለወንድ ጾታ የተደነገገው የሴቷንም ጾታ ያካትታል።

# ምዕራፍ ሁለት
# የሕገ መንግሥት መሠረታዊ መርሆች

## አንቀፅ 8
## የሕዝብ ወሳኝነት

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ የአፋር ሕዝብ የብሔራዊ ክልሉ መንግሥት የበላይ ስልጣን ባለቤት ነው።
2. የብሔራዊ ክልሉ ሕዝብ የበላይነት የሚገለፀው በሚመርጧቸው ተወካዮችና ራሳቸው በቀጥታ በሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ ተሣትፎ ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 9
## የሕገ መንግሥቱ የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ

1. ይህ ሕገ መንግሥት የብሔራዊ ክልሉ የበላይ ሕግ ነው። ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም የባለሥልጣን ውሣኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚነት አይኖረውም።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፣ የመንግሥት አካላት፣ የፓለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስለጣኖቻቸው ይህንን ሕገ መንግሥት የማክበርና የማስከበር እንዲሁም ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ የመሆን ሃላፊነት አለባቸው።
3. በዚህ ህገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥትን ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነው።

## አንቀፅ 10
## ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገሠሱ ናቸው።
2. በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው።

## አንቀፅ 11
## የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው
2. መንግሥታዊ ሐይማኖት አይኖርም
3. መንግሥት በሐይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፣ ሐይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

www.abyssinialaw.com

### አንቀፅ 12
### የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ መንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት።
2. ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሣው ይችላል ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
3. ማንኛውም ኃላፊ ወይም የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል።

## ምዕራፍ 3
## መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

### አንቀፅ 13
### ተፈፃሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕግ አውጭ፣ የሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካላት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ሃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።
2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት የመሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ድንጋጌዎች ፌደራላዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፑብሊክ ኢት፧ጵያ ከተቀበላቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶትች ሰነዶችና መርሆች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ።

## ክፍል አንድ
## ሰብአዊ መብቶች

### አንቀፅ 14
### የሕይወት፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብአዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ የሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 15
## በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው። ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም።

## አንቀፅ 16
## የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።

## አንቀፅ 17
## የነፃነት መብት

1. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ስርዐት ውጭ ነፃነቱን አያጣም።
2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዐት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሠር አይችልም።

## አንቀፅ 18
## ኢ–ሰብአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም ለማንኛውም አላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው።
3. ማንኛውም ሰው በሃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በሃይል ተገዶ "ወይም" ግዴታን ለማሟላት የሚለው ሃረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም።
   ሀ. ማንኛውም እስረኛ በእስር ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሠራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሠራውን ማንኛውም ሥራ፣
   ለ. ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠውን አገልግሎት፣

www.abyssinialaw.com

ሐ. የማሕበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ የሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥን ማንኛቸውም አገልግሎት፣

መ. በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈፀምን ማንኛውም የኢኮኖሚና የማህበራዊ የልማት ሥራ።

## አንቀፅ 19
## የተያዙ ሰዎች መብት

1. ወንጀል ፈፅመዋል በማባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ምክንያቶቹ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው።
2. የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት ያላቸው ስለመሆኑና ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው።
3. የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው። ይህም ጊዜ ሰዎች ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረቡም በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለየቶ እንዲገለፅላቸው መብት አላቸው።
4. የያዛቸው የፖሊስ መኮንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜ ገደብ መሰረት ፍርድ ቤት በመቅረብ የተያዙበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አላቸው። ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዙት ሰዎች በጥበቃ ስር እንዲቆዩ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቀድ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለስልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዙት ሰዎች በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ያላቸውን መብት የሚያከብር መሆን አለበት።
5. የተያዙት ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማንኛውም ማስረጃ እንዲያመጡ አይገደዱም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።
6. የተያዙት ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው ሆኖም በሕግ በተደነገገ ልዩ ሆኔታዎች መሠረት ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 20
## የተከሰሱ ሰዎች መብት

1. የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልፅ በሆነ ችሎት የመስማት መብት አላቸው። ሆኖም የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት የሕዝቡን የሞራል ሁኔታና የአገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል።
2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸውና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት አላቸው።
3. ማንኛውም ተከሳሽ በፍርድ ሂደት ባለበት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አለቸው።
4. የተከሰሱት ሰዎች የቀረበባቸውን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት ወይም ምስክሮችቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው። እንዲሁም ለመከላከል የሚያስችላቸው ማንኛውም ማስረጃ የማቅረብ ወይም እንዲቀርብላቸው የማድረግና ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።
5. የተከሰሱ ሰዎች በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ የማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው።
6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው።
7. የፍርዱ ሂደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው።

## አንቀፅ 21
## በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት

1. በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አለቸው።

2. ከትዳር ጓደኞቻቸውና ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከሀይማኖት አማካሪያቸው፣ ከሃኪማቸውና ከሕግ አማካሪያቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኙአቸው ዕድል የማግኘት መብት አለቸው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 22
## የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የከተሰሰበትን ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙን ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈፀመ ጊዜ ለወንጀሉ ተፈፃሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛው ሰው ላይ አይወሰንም።
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 1 ድንጋጌ ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሽ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኃላ የወጣው ሕግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## አንቀፅ 23
## በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግና ሥነሥርዐት ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጐች መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

## አንቀፅ 24
## የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሥፍራ በሰብአዊ ፍጡርነቱ እወቅና የማግኘት መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው ሰብዐዊ ክብሩንና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው።
3. ማንኛውም ሰው የራሱን ሰብአዊና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሳደግ መብት አለው።

## አንቀፅ 25
## የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው። በመካከላቸው ማንኛውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 26
## የግል ሕይወት የመከበርና የመጠቀም መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመበርበር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል።
2. ማንኛውም ሰው በግል የሚፅፋቸውና የሚፃፉለት በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም።
3. የመንግሥት ባለስልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው። አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን፣ የሕዝብ ሰላምን፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ ለመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነቶች በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሠረቱ ዝርዝር ሕጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም።

## አንቀፅ 27
## የሃይማኖት፣ የህሊናና የእምነት ነፃነት

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና የሀይማኖት ነፃነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት መያዝ ወይም የመቀበል ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ የመከተል የመተግበር የማስተማር ወይም የመግለፅ መብትን ያካትታል።
2. በፌደራል ሕገ መንግሥት አንቀፅ 90 ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸውን የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ።
3. ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በሃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም።
4. ወላጆችና ሌሎች ሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የሃይማኖታቻውንና የመልካም ስነምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው።
5. ሃይማኖትና እምነትን የመግለፅ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ የሌሎች ዜጎች መሰረታዊ መብቶች፣ ነፃነቶችና መንግስት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 28
## በሰብዕና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የሀገሪቱ ሕጎች " በሰው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች" ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች በተለይ የሰው ዘር ማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙት ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በሕግ አውጭው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምህረት በይቅርታ አይታለፍም።

# ክፍል ሁለት
## ዲሞክራሲያዊ መብቶች

## አንቀፅ 29
## የአመለካከት፣ ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለከከት ለመያዝ ይችላል።
2. ማንኛውም ሰው ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለፅ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት፣ በስነጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውም አይነት መረጃና ሀሳብን የመሰብሰብ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል።
3. የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የሥነጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል።
   ሀ. የቅድሚያ ምርምራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑ፣
   ለ. የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት መሆኑ፣
4. ለዲሞክራሲያዊ ስርዐት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሰራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል።
5. በክልሉ ውስጥ በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄደው ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።

www.abyssinialaw.com

6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው " የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም። በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ህጋዊ ገደቦች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዐዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናል።

7. ማንኛውም ሰው ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦች ጥሶ ከተገኘ በህግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።

## አንቀፅ 30
## የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ከቤት ውጪ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ስርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ።
2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ክሶች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም፡

## አንቀፅ 31
## የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ሕገ መንግሥታዊ ሥርዐቱን በህገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት መንገድ የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 32
## የመዘዋወር ነፃነትና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት መብት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀፅ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በሀጋዊ መንገድ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው በመረጠው የክልሉ አከባቢ የመዘዋወርና መኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ ሰርቶ የመኖር፣ ሀብት ንብረት የማፍራት፣ የመሸጥ፣ የማስተላለፍ፣ የማውረስ እና የመያዝ እንዲሁም በፈለገ ጊዜ ከክልሉ የመውጣት መብት አለው።

## አንቀፅ 33
## የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር በብሔር ብሔረሰብ በሃይማኖት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው። በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ ዕኩል መብት አላቸው። በፍችም ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ።
2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ይመሰረታል።
3. ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው ከሕብረተሰቡና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።
4. በባህል በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በሃይማኖታዊ ወይም በባህላዊ ሥርአቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል።
5. ይህ ሕገ መንግሥት የግል የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖታዊ በባህላዊ ሥርዐት መሠረት መዳኘትን አይከለከልም ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 34
## የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ሕገ መንግሥት በአረጋገጠላቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።
2. ሴቶች በዚህ ሕገመንግሥት በተደነገገው መሠረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።

www.abyssinialaw.com

3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት ሲታዩ በመቆየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን የታሪክ ጠበሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ጠባሳ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው። ከዚሁ አኳያ የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና በግል ተቋማት ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው።
4. ሴቶች ከጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶች ተፅዕኖ ለመላቀቅ ያላቸውን መብት መንግሥት ማስከበር አለበት። ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው።
5. ሴቶች የቅጥር፣ የስራ ዕድገት፣ እኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው።
   ሀ. የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው። የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሠራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት ፣ የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል።
   ለ. የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሠረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል።
6. ሴቶች በእርግዝና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው።
7. ሴቶች ንብረት የማፍራት የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው። በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች እኩል መብት አላቸው። እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው።
8. ሴቶች በብሔራዊ ክልሉ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።

## አንቀፅ 35
## የሕፃናት መብት

1. ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት።
   ሀ. በህይወት የመኖር፣
   ለ. ስምና ዜግነት የማግኘት፣
   ሐ. ወላጆችን ወይም በህግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

www.abyssinialaw.com

መ. ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርት፣ በጤናው በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎችን እንዲሰራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣

ሠ. በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ከጭካኔና ኢሰብአዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን፣

2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወስዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጐት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች፣ ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት።

3. ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግስት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች በመንግሥት ወይም የግል እጓለማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው።

4. ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ውስጥ ከተወለዱ ሕፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው።

5. መንግስት ለእጓለማውታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል።

## አንቀፅ 36
## ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከተው ውሳኔ ወይም ፍርድ፣
   ሀ. ማንኛውም ማህበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል
   ለ. ማንኛውም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 37
## የአፋር ሕዝብ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት

የአፋር ሕዝብ በኢት¿ጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው። በዚህ መሠረት የአፋር ሕዝብ፡፡

1. የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብና የማበልፀግ የማሳደግ፣ ባህሉን የመግለፅ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አለው።
2. በራስ መልከዓ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራስን ጉዳይ በራስ የመጨረስ፣ በራስ የማስተዳደርና እንዲሁም በፌደራላዊ መንግስት ውስጥ በነፃነት፣ ተገቢና ፍትሀዊ የሆነ የውክልና አግባብ ውጤታማ ተሳትፎ ለማድረግ መብት አለው።
3. የአፋር ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር መብት፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልከዓምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግስታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል መንግስት አስተዳደር ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል።
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እስከ ንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሱት መብቶች ታገዱ፣ ተረገጡ፣ ወይም ተሸራረፉ ብሎ ባመነበትና ባንድነት ስር ሆኖ ሊያስተካክላቸው ባልቻለበት ጊዜ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 39 በተደነገገው መሠረት የራስን ዕድል በራስ እስከ መገንጠል ድረስ የመወሰን መብቱን ተግባራዊ ያደርጋል።
5. የአፋር ሕዝብ የራሱን ዕድል የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያለ መብት በሥራ ላይ የሚውለው፡፡
   ሀ. የመገንጠል ጥያቄ በሕግ አውጭ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ የድምፅ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲያረጋግጥ
   ለ. የፌደራሉ መንግሥት የሕዝብ ምክር ቤቱ የመገንጠል ውሳኔ በደረሰው በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሕዝብ ውሳኔ እንዲያካሂድ ሲያረጋግጥ።
   ሐ. የመገንጠል ጥያቄ በሕዝብ ውሣኔ በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ
   መ. የፌዴራሉ መንግሥት መገንጠሉ ለመረጠውን የአፋር ብሔሪዊ ክልለ ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብ
   ሠ. በሕግ በሚወስነው መሠረት በፌዴራል መንግሥትና ለመገንጠል የወሰነው የአፋር ብሔራዊ ክልል መንግሥት መካከል የንበረት ክፍፍል ሲደረግ ነው።
6. በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ “ የአፋር ሕዝብ“ ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያለው፣ የአፋርኛ ቋንቋ የሚናገር፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለኝ ብሎ የሚያምንና በአብዛኛው በተያያዘ መልክአምድር የሚኖር ሕብረተሰብ ነው።

www.abyssinialaw.com

# አንቀፅ 38
## የንብረት መብት

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል፣ ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ ለሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም፣ ወይንም የሌሎችን ዜጎች መብቶችን እስካልተቃረኑ ድረስ ንብረት የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም ለሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶች ያካትታል።
2. በዚህ አንቀፅ ዓላማ " የግል ንብረት" ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው አገር አቀፋዊ ወይም ክልላዊ ማሕበራት፣ ወይም አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤቶች፣ እንዲሆኑ በተፈቀደላቸው ማሕበረሰቦች በፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው።
3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የክልሉ ሕዝብ የጋራ ንብረት ነው።
4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
5. በክልሉ የሚገኙ አርብቶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
6. የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ የሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩም በሕግ ይወሰናል።
7. ማንኛውም ሰው በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሣ ክፍያ የመጠበቅ መብትን ያካትታል ዝርዝር አፈፃፀሙ በሕግ ይወሰናል።
8. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠቀበ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረቱን ለመውሰድ ይችላል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 39
## የኢኮኖሚያዊ፣ የማሕበራዊና የባህል መብቶች

1. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪና በክልሉ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው።
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው።
3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄደው ማህበራዊ አገልግሎት በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው።
4. የክልሉ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመደባል።
5. የክልሉ መንግስት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል።
6. የክልሉ መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፓሊሲ ይከተላል እንዲሁም በሚካሄደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።
7. የክልሉ መንግሥስት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።
8. አርብቶ አደሮችና ገበሬዎች በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውንና ለብሔራዊ ሃብት ካደረጉት የምርት አስተዋፅኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ወጤቶቻቸው የማግኘት መብት በሚተልምበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት።
9. የክልሉ መንግሥት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ስነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋፅኦ የማድረግ ሃላፊነት አለበት።
10. የክልሉ አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች የብድር አገልግሎት እንዲሁም ለእንስሳት እርባታና ግብአቶች ያመች ዘንድ መንገድ፣ ገበያና ሌሎች መሠረተ ልማቶች እንዲዘረጉ ልዩ ጥረት ያደርጋል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 40
## የሠራተኛ መብት

1. የፋብሪካና የአስተዳዳር ሠራተኞች የእርሻ ሠራተኞች፣ ገበሬዎች ሌሎች የገጠር ሠራተኞች ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች
   ሀ. የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው፡ ይህ መብት የሠራተኛ ማህበራትንና ሌሎች ማህበራትን የማደራጀት ከአሰሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል።
   ለ. በንዑስ አንቀፅ /1/ የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ የማቆም ጨምሮ ቅሬታ የማሰማት መብት አላቸው።
   ሐ. በንዑስ አንቀፅ /ሀ/ እና /ለ/ መሠረት እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ።
   መ. ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።
2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።
3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዐት ይደነገጋል።

## አንቀፅ 41
## የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታዎችን የማሻሻልና የማያቋርጥ ዕድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።
2. የክልሉ ነዋሪዎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ በሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።
3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች ዕድገትን ሠረታዊ ፍላጎት ማማሏት ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 42
## የአከባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው።
2. የክልሉ መንግሥት በሚያካሄዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ ዕርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው።

# ምዕራፍ አራት
# የክልሉ መንግሥት አደረጃጀትና የስልጣን ክፍፍል

## አንቀፅ 43
## የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

1. ክልሉ በቀበሌ፣ በወረዳ ወይም በከተማ እንዲሁም በክልል ምክር ቤት የተዋቀረ ነው። ይሁን እንጂ የክልሉ ም/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር እርከኖች ሊያዋቅርና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን ይችላል።
2. የክልሉ ነዋሪ የሆነው የአርጎባ ህዝብ የልዩ ወረዳ ውክልና በዚሁ ህገ መንግስት ተረጋግጧል።

## አንቀፅ 44
## የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

1. የክልሉ መንግሥት ህግ አውጪ አካል የክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱ ለወከለው ህዝብ ነው።
2. የክልሉ ከፍተኛ የህግ አስፈጻሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የክልሉ የዳኝነት ስልጣን ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 45

## የክልሉ መንግስት ስልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ውስጥ በግልጽ ተለይተው ለፌዴራሉ መንግሥት ወይም ለፌደራሉ መንግስትና ለክልሉ መንግስት በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጭ ያለ ማናቸውም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግስት ተግባር ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ክልላዊ መንግስቱ፡

   ሀ. የክልሉን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ ዕቅድ ያወጣል ያስፈጽማል።

   ለ. የክልሉን ህገ መንግሥትና ሌሎች ህጐችን ያወጣል ያስፈፅማል።

   ሐ. የፌደራሉ መንግሥት በሚያወጣው ህግ መሠረት መሬትንና የተፈጥሮ ሃብትን ያስተዳድራል፡

   መ. ራስን በራስ ማስተዳደር ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል የህግ የበላይነት የሠፈነበትን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል። የኢት¿ጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት ይህንን ህገ መንግስት ይጠብቃል፣ ይከታተላል።

   ሠ. በክልሉ ውስጥ መሠረታዊ የእንስሣት ሀብት ልማትና ግጦሽ ልማት በአጠቃላይ በግብርና ልማት ስራዎች ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ስራዎቹ በአግባቡ መከናወናቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።

   ረ. የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ህግ ያወጣል ያስፈጽማል፣ ይህን በማያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት የስልጣናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

   ሰ. የክልሉን ፓሊስ ኃይል ያደራጃል ይመራል የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል።

   ሸ. የኢትዩጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀጽ 28ንዑስ አንቀጽ 1 እና የዚህ ህገመንግሥት አንቀጽ 28 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በህግ መሠረት ምህረት ወይም ይቅርታ ያደርጋል።

   ቀ. ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶች ይጥላል ይሰበስባል የክልሉን በጀት ያዘጋጃል ያፀድቃል ያስተዳድራል።

   በ. በክልል መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የስራ ግብር ይጥላል ይሰበስባል።

   ተ. የመሬት መጠቀሚያ ክፍያን ይወስናል ይሰባሰባል።

   ቸ. የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል ይሰበስባል።

www.abyssinialaw.com

ነ. በክልሉ በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል ይሰበስባል በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል።

ኘ. በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ በህጉ መሠረት ይሠበስባል።

ኀ. ከፌዴራል መንግስት ጋር

1. ጋራ ከሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር የሥራ ግብር የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በህጉ መሠረት ይካፈላል።
2. ከድርጅቶች የንግድ ትርፍና ላይና ከባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በህጉ መሠረት ይካፈላል።
3. ከከፍተኛ የማዕድን ስራዎችና ከማንኛውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በህጉ መሠረት ይካፈላል።

አ. በክልል መስተዳድሩ አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወሰናል ይሰባሰባል።

ከ. ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያን ይወሰናል።

ወ. በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሊከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አወጅ አውጥቶ በስራ ላይ ያውላል።

## ምዕራፍ አምስት
## <u>ስለ ክልሉ ም/ቤት</u>

### አንቀጽ 46
### <u>ስለክልሉ ምክር ቤት አባላት</u>

1. የክልሉ ምክር ቤት አባላት ነፃ ቀጥተኛ ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በህዝብ ይመረጣሉ።
2. የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
3. የምክር ቤቱ አባላት የመላው የክልሉ ህዝብ ተወካዮች ናቸው። ተገዥነታቸውም

   ሀ. ለህገ መንግሥቱ፣

   ለ. ለመረጣቸው ህዝብና

   ሐ. ለህሊና ብቻ ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

4. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምፅ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም አስተዳደራዊ እርምጃ አይወሰዳበትም።
5. ማንኛውም የክልል ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጸም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም በወንጀል አይከሰስም።
6. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ህዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በህጉ መሠረት ከምክር ቤት አባልነት ይወገዳል።

## አንቀፅ 47
## የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ምክር ቤት በዚህ ህገ መንግስት መሠረት የክልሉ ህግ አውጪ አካል ነው።
2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በብሔራዊ ክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ስር የሰፈረው አጠቃላይ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በተለይ የሚከተሉት ስልጣንና ሃላፊነቶች ይኖሩታል።
   ሀ. በዚህ ህገመንግሥት መሠረት የፌደራሉን ህገመንግስትና ሌሎች ህጎችን የማይጻረሩ ልዩ ልዩ ህጎች ያወጣል።
   ለ. የህዝብን ብዛት የክልሉን ስፋትና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ አመት ውስጥ በማስገባት በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለታካ ስልጣን ባለቤት ነው።
   ሐ. የፌደራሉ መንግስት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጐራባች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ጋር የሚደረጉ ስምምነቶችን ያፀድቃል።
   መ. የራሱን አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ ይመርጣል። ለምክር ቤቱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ይሰይማል።
   ሠ. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ርዕሰ መስተዳድሩን በምርጫ ይሰይማል በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን ምክትል መስተዳድርና የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያፀድቃል።
   ረ. በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ዋና ኦዲተሩንና ምክትል ዋና ኦዲተሩን ይሾማል።
   ሰ. የክልል፣ የዞንና የወረዳ የዳኝነት አካላትን ያቋቁማል።
   ሸ. የኦዲትና የቁጥጥር አካሉን ያቋቁማል።
   ቀ. በህጉ መሠረት ምህረት ያደርጋል።
   በ የክልሉን ሠላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ያወጣል የፀጥታና የፖሊስ ሃይሉን ያቋቁማል።
   ተ. የብሔራዊ ክልሉን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞች ያፀድቃል።

www.abyssinialaw.com

ቸ. የብሔራዊ ክልሉን የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ህጐች ያወጣል የክልሉን በጀት መርምሮ ያፀድቃል፡፡

ነ. ለማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት ለኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠንና ለዲሞክራሲያዊ ስልጣን ግንባታ አስፈለጊ የሆኑ ተቋማትን ያቋቁማል፡፡

ኘ. ለክልሉ መንግስት በተከለለው የገቢ ምንጭ በክልሉ ውስጥ ግብርና ታክስ ይጥላል፡፡

አ. የክልል መስተዳድሩን የሠራተኛ አስተዳደር የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ህግ ያወጣል፡፡

ከ. በዚህ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 2 (ወ) ሥር ለክልሉ መንግስት በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፡፡

ወ. በተለይ በግብርና ልማት ስር የእንስሳት ሀብት ልማት እና የግጦሽ ልማት ወዘተ የስራ እንቅስቃሴዎች በመስተዳድር ምክር ቤቱ እና በቀጥታ ጉዳዩ በሚመለከተው አስፈፃሚ አካል እየተከናወኑ መሆናቸውን ይከታተላል፡፡

ኀ. የሀገሪቱንና የክልሉን ህግጋተ መንግስታት፣ አዋጆችና ሌሎች ህጐችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር የማስፈጸሚያ ደንቦችን ያወጣል፡፡

ዐ. የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግስት ባለስልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፡፡ የአስፈጻሚውን አካል አሠራር ይመረምራል፡፡

## አንቀፅ 48
## ስለ ክልሉ ምክር ቤት

1. የክልሉ ምክር ቤት የራሱ ፅህፈት ቤት ይኖረዋል፡፡
2. የፅህፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል፡፡

## አንቀፅ 49
## ስለ ምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ አሰያየምና የስራ ዘመን፡

1. የክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ በዚህ ህገመንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (መ) መሠረት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየም ሆኖ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው፡፡
2. የአፈ ጉባኤው የሥራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 50
## የአፈጉባኤ ስልጣንና ተግባር

የክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በዚህ ህገመንግስት መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል ይመራል፡፡
2. ምክር ቤቱን በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፡፡
3. የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፡፡
4. ምክር ቤቱ በአባሎች ላይ እንዲወስድ የወሰነው የዲስፒሊን እርምጃ ያስፈጽማል፡፡
5. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀፅ 51
## የምክትል አፈጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

ምክትል አፈጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈጉባኤውና ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ፡፡

1. በአፈጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡
2. አፈጉባኤው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፡፡

## አንቀፅ 52
## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የክልሉ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ከሁለት ሶስተኛው በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ የስብሰባው ምልአተጉባኤ ይሆናል፡፡ የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይተላለፋል፡፡
3. የክልሉ ምክር ቤት አባላት የሚመረጡት ለአምስት ዓመታት ነው የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል፡፡ የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፡፡
4. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛው በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ በጠየቁ ጊዜ አፈጉባኤው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡

www.abyssinialaw.com

5. የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል። ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ወይም በክልሉ አስፈጻሚ አካል በተጠየቀና በምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉት ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊደርግ ይችላል።

## አንቀፅ 53
## የምክር ቤቱ ውሳኔዎችና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓቶች

1. በዚህ ህገ መንግስት ውስጥ ተገልጾ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይሆናል።
2. ምክር ቤቱ ውስጣዊ አሠራሩንና የህግ አወጣጡን ሂደት አስመልክቶ ዝርዝር ደንቦችን ሊያወጣና በሥራ ላይ ሊያውል ይችላል።

# ምዕራፍ ስድስት
# የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የህግ አስፈፃሚ አካል መቋቋም

## አንቀፅ 54
## የአስፈፃሚነት ሥልጣን

1. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠው ለርዕሰ መስተዳድሩና ለመስተዳድር ምክር ቤት ነው።
2. ርዕሰ መስተዳድሩና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነታቸው ለብሔራዊ ክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት በመንግስት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ ለሚፈፅሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀፅ 55
## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አወቃቀር

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድሩ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የአስፈፃሚ ቢሮዎች ኃላፊዎችና በህግ በሚወሰነው መሠረት ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነው።
2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ርዕሰ መስተደድሩ ነው።
3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩነው።
4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወሰነው ውሳኔ ለክልሉ ም/ቤት ተጠሪ ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 56
## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የፌደራሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በክልሉ ምክር ቤትና በፌደራሉ መንግስት የወጡ ህጐችና የተላለፉ ውሳኔዎች በክልሉ ውስጥ በስራ መተርጐማቸውን ያረጋግጣል።
2. የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የአስፈፃሚ አካላትና የሌሎች ተቋማት አደረጃጀት ይወስናል። ስራቸውን ይከታተላል በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል።
3. የክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ይነድፋል፣ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል የተወሰነውንም ያስፈፅማል።
4. በክልሉ ውስጥ ህግና ስርዕት መከበሩን ያረጋግጣል በህግ መሠረት ይቅርታ ያደርጋል።
5. የክልሉ ም/ቤት በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችና መመሪያዎች ያወጣል።
6. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ረቂቅ አዘጋጅቶ ለክልል ም/ቤት ያቀርባል።
7. በዚህ ህገ መንግሥት አንቀፅ 47 ንዑስ አንቀፅ 2 (ጠ) ሥር ለክልል ምክር ቤት አስቀድሞ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ በስራ ላይ ያውላል።
8. የክልሉ የአርብቶ አደር የኑሮ ሁኔታ የተሻለና ከዐላ ቀር አሠራር የሚላቀቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል።
9. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀፅ 57
## የከተማ ምክር ቤትን ስለማቋቋም

የክልል ም/ቤት የከተሞችን የእድገት ደረጃና ልዩነትን ባገናዘበ መልኩ የከተማ ም/ቤቶችን ያቋቁማል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 58
## የርዕስ መስተዳድሩ አስያየምና የሥራ ዘመን

1. ርዕስ መስተዳድር በክልሉ ምክር ቤት ውስጥ በአብላጫ መቀመጫ ባገኘው የፓለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት ከክልሉ ምክርቤት አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል።
2. በዚህ ህገ መንግስት በሌላ አኳኃን ካልተወሰነ በስተቀር የርዕስ መስተዳድሩ የስራ ዘመን የብሔራዊ ክልል ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 59
## የርዕሰ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባር

1. ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ መስተዳድር ስራ መሪ፣ የመስተዳድር ምክር ቤቱ ሠብሳቢና የብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ነው
2. ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕስ መስተደድሩ።
   ሀ. የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል ያስተባብራል ይወክላል።
   ለ. የክልሉ መንግስት ህግ አውጪና ህግ አስፈፃሚ አካላት በየበኩላቸው መክረው ያፀደቋቸውን አዋጆችና ደንቦች " በአፋር ነጋሪት ጋዜጣ " ይታወጁ ዘንድ በአስራ እምስት ቀናት ውስጥ ፊርሞ ይልካል።
   ሐ. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣቸውን ፓሊሲዎች፣ ደንቦች መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈፃሚነት ይከታተላል።
   መ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተር መርጦ ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስሾማል።
   ሠ. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የሆኑ አስተዳዳሪዎችንና የመስተዳድር ም/ቤት አባላት የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎችን ሹመት ለክልል ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል።
   ረ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ፊደል ተራ ቁጥር "መ" እና "ሠ" ሥር የሠፈረው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜና ሁናቴ ከምክትል ርዕሰ ምስተዳድሩ፣ከዞን አስተዳዳሪዎች በመለስ ያሉትንና ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የሥራ ኃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሰራል።
   ሰ. ከክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ውጭ የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎች ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች፣ ኮሚሽነሮች መምሪያ ኃላፊዎችና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች መርጦ ይሾማል።
   ሸ. የብሔራዊ ክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ሕግና ሥርዕትን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል።
   ቀ. በክልሉ የሚገኙትን የበታች የአስተዳደር እርከኖች ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል ይቆጣጠራል።
   በ. በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።
   ተ. ዝርዝሩ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሠን ሆኖ አስፈላጊነታቸው እየታየ በተመረጡ ስፍራዎች የክልል መስተዳድሩን የሚወክሉና

www.abyssinialaw.com

ለወረዳዎች ሁለተናዊ ድጋፍ የሚሰጡ የአስተዳደር አካባቢ ተጠሪ ጽሕፈት ቤቶች ያቋቁማል። አስተዳዳሪዎችንና ሌሎች የስራ ኃላፊዎችን ይሰይማል።

## አንቀፅ 60
## የምክትል ርዕስ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩከብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት መካከል በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በብሔራዊ ክልሉ ምክር ቤት የሚሾም ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ. በርዕሰ መስተደድሩና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
   ለ. ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።
2. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነት፥ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነው።

## አንቀፅ 61
## የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት

1. ርዕሰ መስተዳድሩ በህገ መንግስቱ የተሰጠውን ሥልጣን ለመወጣት ያስችለው ዘንድ የራሱ የሆነ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።
2. የርዕሰ መስተደድሩ ጽሕፈትቤት የመስተዳድሩ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል።
3. የጽሕፈት ቤቱ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 62
## ስለ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ አስተዳደራዊ ተቋማት መቋቋም

1. የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና አስተዳደራዊ የእለት ተእለት ሥራዎች የሚያከናውኑ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ልዩ ልዩ ቢሮዎች ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ተቋማት እንዳስፈላጊነታቸው ይቋቋማሉ።
2. የቢሮዎችና ሌሎች ከፍተኛ ተቋማት ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ለመስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ያልሆኑ ቢሮዎችና ሌሎች ተቋማት ተጠሪነት ከተቋቋሙበት አላማና

www.abyssinialaw.com

ከሚያስፈፅሙት ተልዕኮ ጋር አግባብነት ላላቸው የክልሉ መንግስት የበላይ አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች ይሆናል፣ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 63
## የሽማግሌዎች ጉባኤ ስለማቋቋም

የክልሉ ምክር ቤት እንደ አስፈላጊነቱ የአገር ሽማግሌዎች ጉባኤ በተለያየ እርከን ያቋቁማል ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## ምዕራፍ ሰባት
## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ሥልጣን

## አንቀፅ 64
## ስለነፃ የዳኝነት አካል መቋቋም

1. የክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ህገ መንግስት ተቋቁሟል
2. የዳኝነትን ሥልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በህግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጪ የሚደረግና በህግ የተደነገገውን የዳኝነት ሥርዕት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም።

## አንቀፅ 65
## ስለባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ የዳኝነት አካል

በዚህ ሕገ መንግስት አንቀፅ 64 ንዑስ አንቀፅ 2 ስር የተደነገገው እንዳተጠበቀ ሆኖ ይህ ህገ መንግስት ከመፅደቁ በፊት በመንግስት ዕውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካል በዚህ ህገመንግስት ዕውቅና አግኝተው ይደራጃሉ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 66
## የዳኝነት ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው።
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል፣ ከማናቸውም የመንግስት አካል ባለስልጣን ወይም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው።

www.abyssinialaw.com

3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ። ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።
4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በህግ የተወሰነው የጡረታ እድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ስራው አይነሳም።
   ሀ. የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲሲፒሊን ህግ መሠረት ጥፋት ፈፅማል ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወሰን ወይም
   ለ. በህመም ምክንያት የዳኝነት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና
   ሐ. የጉባኤው ውሳኔ ለክልሉ ምክር በት ቀርቦ በአባላቱ የአብላጫ ድምፅ ሲደገፍና ሲፀድቅ
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሠረት አንድ ዳኛ ከዳኝነት ሥራው የሚያስነሳው ጥፋት ፈፅሟል ብሎ ጉባኤው ከወሰነበት ጉዳዩ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ እስኪታይ ድረስ ከዳኝነት ስራው ታግዶ መቆየት ይኖርበታል።
6. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም።

## አንቀፅ 67
## የፍርድ ቤቶች አዳረጀጀትና ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና በወረዳ ፍርድ ቤቶች ይደራጃል። የወረዳ ፍርድ ቤት የክልሉ የበታችና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነው።
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት
   ሀ. ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ስልጣን፣
   ለ. በፌደራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራሉ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን፣
   ሐ. ማናቸውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ሲኖረበት በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካለው ክልላዊ ስልጣን በተጨማሪ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሆን ይዳኛል።
4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል።

www.abyssinialaw.com

5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌደራሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል።
6. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።
7. የክልሉ ፍርድ ቤቶች በውክልና የሚፈፅሙትን ፌዴራላዊ የዳኝነት ተግባር ለማከናወን የሚያወጡትን ገንዘብ ወጪ በተመለከተ ከፌዴራል መንገስት ማካካሻ እንዲሰጣቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀርባል።

## አንቀፅ 68
## ስለ ዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።
2. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች እና የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ።
3. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌደራል ዳኞች አስተዳዳር ጉባኤ በእጩዎች ላይ ያለውን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልል ምክር ቤት የማቅረብ ሃላፊነት አለበት። ሆኖም የፌደራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተጠየቀውን አስተያየት በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የእጩ ዳኞችን ሹመት ያፀድቃል።

## አንቀፅ 69
## ስለክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምፅ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይቋቋማል።
2. የክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ጉባኤውን በሊቀመንቀበርነት ይመራል።
3. የጉባኤው አባላት ዝርዝር ስብጥር ስልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 70
## ህገ መንግስቱን ስለመተርጎም

1. በክልሉ ውስጥ የህገ መንግስታዊ ክርክር ጉዳይ ወይም የትርጉም ጥያቄ ሲነሳ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የወረዳ ምክር ቤቶች የተመረጡ አንዳንድ አባላት ተውጣጥቶ የሚሰየም የህገ መንግስት ተረጓሚ ከሚስዮን በዚህ ህገመንግሥት ተቋቁመዋል።
2. ኮሚሲዮኑ የክልሉ ህገመንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ህገመንግስታዊ ጉዳዮች ላይ መክሮ በስልሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚቋቋመው ኮሚሲዮን አገልግሎት ዘመን አምስት ዓመት ሲሆን ህገመንግስታዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ይሰበሰባል።
4. ኮሚሲዮኑ የራሱን ሰብሳቢና ፀሀፊ ከአባላቱ መከከል መርጦ ሥራውን የሚያከናውን ሲሆን ለሥራው የሚያስፈልገው የጽህፈት ቤት አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ ከክልሉ ምክር ቤት ያገኛል።

## አንቀፅ 71
## የህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

1. የክልሉ ህገመንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ህገ መንግሥት ተቋቋመዋል።
2. የክልሉ ህገመንግስታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አስራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።
   ሀ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት - - - - ሰብሳቢ
   ለ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት - - - - ምክትል ሰብሳቢ
   ሐ. በክልል መስተዳድር ፕሬዝዳንት አቀራቢነት በብሔራዊ ክልል ምክር ቤት የሚሾሙና በሙያ ብቃታቸውና በስነ ምግባራቸው የተመሠከረላቸው ስድስት የህግ ባለሙያዎች - - - - አባላት
   መ. በአፈጉባኤው አቀራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየሙ 3 ተወካዮች - - - - አባላት

## አንቀፅ 72
## የአጣሪ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ህገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ይህንን ህገመንግሥት መሠረት አድርገው ከብሔራዊ ክልሉ የሚመነጩ ህገመንግስታዊ ጉዳዮች የማጣራት ስልጣን ይኖረዋል። በሚያደርገው ማጣራት መሠረትም የክልሉን ህገ መንግስት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ

www.abyssinialaw.com

ሲያገኘው በጉዳዩ ላይ የራሱን የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል።

2. አጣሪ ጉባኤው በክልሉ መንግስት አባላት የሚወጡ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ ህገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በማናቸውም ሁኔታ ሲነሳና ጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች አማካኝነት ሊቀርብለት ከመረመረና ካጣራ በ፲ላ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኮሚሲዮኑ ያቀርባል።

3. በፍርድ ቤቶች ዘንድ የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ አጣሪ ጉባኤው

   ሀ. የክልሉን ህገመንግሥት መተርጐም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይመልሳል። ሆኖም ባጣሪ ጉባኤው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ባለጉዳይ ይህንኑ ቅሬታውን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ለኮሚስዮኑ በይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

   ለ. የህገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ ሚሰጠውን ህገመንግስታዊ ትርጉም አስናድቶ ለኮሚሽዮኑ ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል።

# ምዕራፍ ስምንት

## ስለ ወረዳ መስተዳድር አደረጃጀት እና ስልጣን

### አንቀፅ 73
### አደረጃጀት እና አሰራር

የወረዳ መስተዳድር ከአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በታች የሚደራጅ የመንግስት አስተዳደር መዋቅር ሆኖ የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል።

1. በስሩ ከተደራጁ ቀበሌዎች በሚወከሉ የሕዝብ ተመራጮች ተዋጽኦ የሚቋቋም የወረዳ ምክር ቤት
2. ከዚሁ ምክር ቤት አባላት መካከል ተመርጦ በሚሰየም የወረዳ ዋና አስተዳደሪ አማካኝነት የሚቋቋም የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት
3. በዚህ ሕገ መንግስት መሠረት የተቋቋመ የወረዳ የዳኝነት አካል

### አንቀፅ 74
### የወረዳ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳ መስተዳድር በተደራጀበት አካባቢ የኢኮኖሚያዊ ልማት እና ማሕበራዊ አገልግሎት እቅዶችን ለማዘጋጀትና ለመወሠንም ሆነ የክልሉ መንግስት አካላት

www.abyssinialaw.com

በየጊዜው የሚያወጧቸውን ፖሊሲዎች፣ ሕጉች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ማናቸውም ስልጣን ይኖረዋል።

2. እያንዳንዱ ወረዳ እራሱን የማስተዳደር፣ አካባቢውን የማልማትና በውስጣዊ ጉዳዮቹ ላይ ውሳኔ የመስጠት መብት እና ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ምክር ቤት ቀጥሎ የሚገኝ የበታች አካል ነው።

## አንቀፅ 75
## ስለወረዳ ምክር ቤት አባላት አመራረጥ እና ተጠሪነት

1. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ወረዳው የተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣሉ።
2. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ይሆናል።

## አንቀፅ 76
## የወረዳ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳ ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ውስጥ ከፍተኛው መንግስታዊ የስልጣን አካል ነው። ተጠሪነቱም ለክልል ምክር ቤት ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ሥር የሠፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ. የወረዳውን ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ አስተዳደራዊ የስራ ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞች ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል።
   ለ. በወረዳው ውስጥ መሠረታዊው የእንስሳት ሀብት ልማት እና የግጦሽ ልማት በአጠቃላይ የግብርና ልማት ስራዎች ወቅቱን ጠብቀው መካሔዳቸውንና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት መከናወኑን ይከታተላል።
   ሐ. ነዋሪውን ሕዝብ ለልማት ስራ በስፋት የሚነሣሣበትንና የሚንቀሣቀስበትን አመች ሁኔታ ይፈጥራል።
   መ. ዝርዝሩ በሕግ የሚወሠን ሆኖ ከምክር ቤት አባላት መካከል አፈጉባኤውን ምክትል አፈ ጉባኤውንና ዋና አስተዳደሪውን በምርጫ ይሠይማል። በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን የወረዳ ምክትል አስተዳደሪ እና የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ተቀብሎ ያፀድቃል።
   ሠ. የራሱን ውስጣዊ የአሠራር ሥነ ስርዓት መወሠኛ መመሪያ ያወጣል።

www.abyssinialaw.com

ረ. ዝርዝሩ በሕግ የሚወሠን ሆኖ የመሬት መጠቀሚያ ታክስን የእርሻ ስራ ገቢ ግብርንና ሌሎች ገቢዎች መሠብሠባቸውን ያረጋግጣል ሌሎች የአገልሎት ታክሶችን እና ክፍያዎችን ይጠቀማል።

ሰ. የራሱን በጀት መርምሮ ያፀድቃል ክልሉ ከሚመድበውና ከሚያስተዳድረው ውጭ ያለውንና የወረዳውን የገቢ ምንጭ ይጠቀማል።

ሸ. የፌዴራሉ እና የክልሉ ሕግጋተ መንግስታትና ሌሎች ሕጐች እንደተጠበቀ ሆነው የወረዳውን ሠላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ አውጥቶ በስራ ላይ ያውላል።

ቀ. የወረዳውን ዋና አስተዳዳሪ ጨምሮ ሌሎች የወረዳውን ባለስልጣናት ለጥያቄ ይጠራል። የአስፈፃሚውን አካል አሠራር ይመረምራል።

## አንቀፅ 77
## ስለምክር ቤቱ አመራር

1. የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት እንዲኖረው ሆኖ ከአባላቱ መካከል ተመርጠው በሚሰየሙ አንድ አፈ ጉባኤና አንድ ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሠናል።

## አንቀፅ 78
## ስለ ወረዳ አፈ ጉባኤ ስልጣን

አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለወረዳው ምክር ቤት ሆኖ

1. ወቅቱን ጠብቆ ምክር ቤቱን ለስብሰባ የመጥራትና ጉባኤውን የመምራት ኃላፊነት ይኖርበታል።
2. ሌሎች የአፈ ጉባኤው ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቶች የክልል ምክር ቤቱን አፈጉባኤ አስመልክቶ በዚህ ሕገመንግስት የተደነገጉት እንደየአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀፅ 79
## ስለ ወረዳ ምክትል አፈ ጉባኤ ስልጣን

ምክትል አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤውና ለወረዳ ምክር ቤት ሆኖ

1. በአፈ ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
2. አፈ ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይቻልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 80
## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜ እና የስራ ዘመን

1. የወረዳ ምክር ቤት በየሶስት ወሩ ይሠበሠባል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከሁለት ሶስተኛው (2/3) መካከል በስብሠባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣ የምክር ቤቱ ውሣኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት አብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።
3. የወረዳ ምክር ቤት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሔዶ ይጠናቀቃል የቀድሞው ምክር ቤት የስራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ስራውን ይጀምራል።
4. የወረዳ ምክር ቤት ስብሠባ በግልጽ ይካሔዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሠባ በማያደርግበት ወቅት አፈጉባኤው አስቸኳይ ስብሠባ ሊጠራ ይችላል። የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሠባ እንዲካሔድ ከጠየቁ አፈ ጉባኤው የምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

## አንቀፅ 81
## ስለ ወረዳ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት

የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት ሊኖረው ይችላል። ሆኖም ምክር ቤቱ የራሱን ጽሕፈት ቤት እስኪያደራጅ ድረስ የመስተዳድር ምክር ቤቱንና የዋና አስተዳዳሪውን ጽሕፈት ቤት እና የቢሮ መገልገያዎች በመጋራት ይሠራል።

## አንቀፅ 82
## ስለ ወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት

1. የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ከፍተኛ ሕግ አስፈፃሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለዋና አስተዳዳሪውና ለወረዳው ምክር ቤት ነው።
2. የወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት የወረዳው አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪ፣ እንዲሁም በወረዳው ውስጥ የተቋቋሙ ዋና ዋና አስፈፃሚ የሴክተር ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች የሚገኙበት አካል ሆኖ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪው ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 83
## ስለወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ. የፌዴራሉና የክልሉ መንግስታት ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ እቅዶች እና ፕሮግራሞች በተቋቋሙበት ወረዳ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።
   ለ. በወረዳው ውስጥ ያሉ አስፈፃሚ አካላትን በበላይነት ያስተባብራል ሥራቸውን ይከታተላል ይመራል።
   ሐ. የወረዳውን አመታዊ በጀት ረቂት ያዘጋጃል፣ ለምክር ቤቱ ያቀርባል ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደረጋል።
   መ. የወረዳውን ሰላምና ፀጥታ ይጥብቃል፣ የወረዳውን የፀጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል ሥራቸውን ያስተባብራል።
   ሠ. የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል። ሲፈትድም ተግባራዊ ያደርጋል።
   ረ. የተፈጥሮ ሃብትን ይጠብቃል፣ ያለማል፣ ይንከባከባል ሕዝቡን ለልማት ስራ በስፋት ያነሣሣል።
   ሰ. በወረዳው ዉስጥ የሚገኝ ማናቸውም ቅርፃ ቅርጽ አስፈላጊው ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት ስለመሆኑ በቅርበት ይከታተላል።
   ሸ. በወረዳው ያለ አርብቶ አደሮችን የኑሮ እንቅስቃሴን ይከታተላል በእንስሣት ሀብት በግጦሽ ልማት እና በመሣሥሉት ጉዳዮች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል ይቆጣጠራል።
   ቀ. በሕግ መሠረት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያ፣ የእርሻ ስራ ገቢ ግብር እና ሌሎች ገቢዎችን ይሠበስባል ተጨማሪ ገቢዎች ስለሚገኙበት ሁኔታ አጥንቶ ለወረዳው ምክር ቤት ለውሣኔ ያቀርባል።
   በ. በወረዳው ምክር ቤት እና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
2. የወረዳ መስተደድር ምክር ቤት አባላት በመንግስታዊ ስልጣናቸው ለማፈጽሙት ተግባር እና ለሚያሣልፉት ውሣኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀፅ 84
## ስለ ወረዳው አስተዳደሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ከወረዳው ምክር ቤት አባላት መካከል አሸናፊ በሆነው ወይም አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት አቅራቢነት በወረዳው ምክር ቤት ይሠየማል።
2. በዚህ ሕገ መንግስት በሌላ አኳኃን ካልተወሠነ በስተቀር የወረዳው አስተዳዳሪ የስራ ዘመን የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 85
## የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነት ለወረዳው ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሆኖ የተሾመበት ወረዳ መስተዳድር ተጠሪና የአስተዳደሩ ስራ መሪ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሠፈረው አጠቃላይ ድርጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው፡
   ሀ. የወረዳውን አስተዳዳሪ ይወክላል ።
   ለ. የወረዳውን መስተዳድር ምክር ቤት ይሠበስባል፡ ይመራል።
   ሐ. የፌዴራሉንና የክልሉ መንግስታት ፖሊሲዎች ሕጐች፣ ደንቦች መመሪያዎችና፣ ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።
   መ. ምክትል አስተዳደሪውን ጨምሮ የወረዳውን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለወረዳው ምክር ቤት አቀርቦ ያፀድቃል።
   ሠ. የወረዳው አስተዳደሩን ልዩ ልዩ ተቋማትና በስሩ የሚገኙትን ቀበሌዎች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል ይመራል ይቆጣጠራል።
   ረ. የወረዳው ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና እቅዶች ወቅቱን ጠብቀው መዘጋጀታቸውን ይቆጣጠራል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል።
   ሰ. የወረዳው ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ሕግና ስርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል።
   ሸ. ለወረዳው ምክር ቤት ለወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት እና ለበላይ የመስተዳድር አካላት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል።
   ቀ. በወረዳው ምክር ቤት እና በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀፅ 86
## የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ

1. የወረዳ አስተዳዳሪው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።
2. በወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውል።

## አንቀፅ 87
## የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ጽሕፈት ቤት

1. የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።
2. የዋና አስተዳዳሪው ጽሕፈት ቤት የወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት በመሆን ጭምር ሊያገለግል ይችላል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሠናል።

www.abyssinialaw.com

# ምዕራፍ ዘጠኝ
## ስለ ቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን

### አንቀፅ 88
### አደረጃጀት እና ተጠሪነት

1. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻው መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን ሲሆን በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ተጠሪነቱ እንደሁኔታው ለታቀፈበት የወረዳ ወይም ከተማ መስተዳደር ይሆናል፡፡
2. የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል።
   ሀ. የቀበሌ ምክር ቤት
   ለ. የመስተዳድር ምክር ቤት
   ሐ. የማህበራዊ ፍርድ ቤት

### አንቀፅ 89
### ስለ ቀበሌ ምክር ቤት

1. የቀበሌ ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥስት መሠረት የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ ተቋቁሟል።
2. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ።
3. የምክር ቤቱ አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ነው።
4. የቀበሌው ምክር ቤት ተጠሪነቱ እንደሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት የከተማ ምክር ቤት ወይም የወረዳ ምክር ቤት ይሆናል።

### አንቀፅ 90
### የቀበሌ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ.89 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሠፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የወረዳው ምክር ቤት እና የወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት በየጊዜው የሚያወጧቸውን መመሪያዎች እና ዕቅዶች በቀበሌው ውስጥ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

www.abyssinialaw.com

2. የበላዩ የሆኑት የአስተዳደር አካላት ከሚያወጧቸው ፖሊሲዎች ሕጐች ደንቦች እና መመሪያዎች ጋር በማይቃረን መንገድ የአካባቢ ማህበራዊ ጉዳይ መመሪያዎችን አውጥቶ በቀበሌው ውስጥ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።
3. ከቀበሌው ምክር ቤት አባላት መካከል አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤና የቀበሌውን አስተዳደሪ ይመርጣል የቀበሌውን መስተዳድር ምክር ቤትም ያደራጃል።
4. በቀበሌው አስተዳዳሪ የሚቀርቡለትን የቀበሌውን ምክትል አስተዳዳሪና የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ያፀድቃል።
5. የበላዩ በሆኑ የአስተዳደር አካላት የሚሰጡትን የማህበረ ኢኮኖሚያዊ ልማት እና አስተዳደሪያዊ እቅዶችንና ፕሮግራሞችን መሠረት በማድረግ የስራ አፈፃፀም መርሀ ግብር ያወጣል አፈፃፀሙንም ይከታተላል።
6. የቀበሌውን የመስተዳድር ምክር ቤትና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን የስራ ክፍፍልና ምደባ ይወስናል።
7. ለቀበሌው ሕዝብ የሚጠቅሙ ሌሎች ተጨማሪ እቅዶችን ያወጣል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል።
8. የቀበሌውን ሕዝብ ለልማት ስራ ያነሣሣል የተፈጥሮ ሀብትን ልማት እና እንክብካቤ ሥራ ይከታተላል።
9. በቀበሌው ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል።

## አንቀፅ 91
## ስለ ቀበሌ ምክር ቤት አመራር

1. የቀበሌ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል በሚመረጡ አንድ አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል።
2. አፈ ጉባኤው ምክር ቤቱን ይሠበስባል ይመራል አጀንዳዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ቃለ ጉባኤ መያዛቸውንና ሰነዶች መጠበቃቸውን ይቆጣጠራል።
3. ምክትል አፈጉባኤው በአፈጉባኤው ተለይተው የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል አፈጉባኤው በማይገኝበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሠራል።

## አንቀፅ 92
## የቀበሌ ምክር ቤት የሰብሰባ ጊዜና የስራ ዘመን

1. የቀበሌ ምክር ቤት መደበኛ ሰብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያካሒዳል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከሁለት ሶስተኛ በላይ የሚሆኑት በስብሠባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል የምክር ቤቱ ውሣኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤት አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።

www.abyssinialaw.com

3. የቀበሌው ምክር ቤት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የስራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሒዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የስራ ዘመን በተጠናቀቀ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።
4. የቀበሌው ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሔዳል ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሠባ እንዲካሔድ ከጠየቁ አፈ ጉባኤው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

## አንቀፅ 93
## የቀበሌ የመስተዳድር ምክር ቤት አወቃቀር

1. የቀበሌ የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት የቀበሌው አስተዳደሪ ምክትል አስተዳዳሪና በቀበሌው ውስጥ ከሚገኙ የማህበራዊ አገልግሎት ሠጭ የመንግስት ተቋማት ሠራተኞች በአባልነት የሚገኙበት የበታች አስፈፃሚ አካል ነው።
2. የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌው አስተዳዳሪና ለቀበሌው ምክር ቤት።
3. የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት በግልና በውል የቀበሌውን አስተዳደር ሥራ ይመራሉ ያስተባብራሉ።
4. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በጋራ ስልጣናቸው ለሚያሣልፉት ውሣኔና ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀፅ 94
## የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል
   ሀ. የቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት የልማት እቅዶችንና ፕሮግራሞችን ያወጣል ለቀበሌው ምክር ቤት እያቀረበ ያፀድቃል በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታታላል ይቆጣጠራል።
   ለ. የገጠር ልማትን ያፋጥናል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንክብካቤና ልማት ስራ እንዲካሔድ ያደርጋል ሕዝቡንም ለልማት ስራ ያነሣሣል ያስተባብራል።
   ሐ. የቀበሌው ሠላምና ፀጥታ እንዲጠበቅ ያደርጋል።
   መ. የስራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል።
   ሠ. በቀበሌው ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
2. የቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤት ዝርዝር የሥራ እቅዶችን የሚነድፈውና አፈፃፀማቸውን የሚከታተለውም ሆነ የሚገመግመው እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው እየተገናኘ ይሆናል።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 95
## ስለቀበሌው አስተዳደሪ አሰያየምና የስራ ዘመን

1. የቀበሌው አስተዳዳሪ ከቀበሌው ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ ይሠየማል።
2. በዚህ ሕገ መንግስት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌ አስተዳዳሪው የስራዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የስራ ዘመን ነው።

## አንቀፅ 96
## የቀበሌ አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

1. የቀበሌዉ አስተዳደሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤትና እንደ ሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት የወረዳ ወይም ከተማ መስተዳደር ሆኖ የቀበሌው ሊቀመንበር መስተዳደሩ ስራ መሪ የቀበሌ የመስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ነው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 ሥር የሠፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌው አስተዳዳሪ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል
   ሀ. የቀበሌውን የመስተዳድር ምክር ቤት ይሠበስባል ይመራል።
   ለ. የበላይ በሆኑት የአስተዳደር አካላት የሚወጡትን ፖሊሲዎች፣ ሕጐች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና እቅዶች ተቀብሎ በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል።
   ሐ. የቀበሌውን ምክትል አስተዳዳሪ እና የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ለቀበሌ ምክር ቤት በማቅረብ ያሾማል።
   መ. በቀበሌው የመስተዳድር ምክር ቤት በቀበሌው ምክር ቤት እና እንደ ሁኔታው በሚመለከተው ከተማ ወይም ወረዳ መስተዳደር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀፅ 97
## የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

የቀበሌው ምክትል አስትዳዳሪ በቀበሌ አስተዳዳሪ ተመርጦ ሹመቱ በቀበሌው ምክርቤት የሚፀድቅ ሆኖ

1. በቀበሌው አስተዳዳሪና በመስተዳድሩ ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።
2. የቀበሌው አስተዳዳሪ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል።
3. የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው አስተዳዳሪና ለመስተዳድሩ ምክር ቤት ነው።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 98
## ስለ ቀበሌ መስተዳደር ጽሕፈት ቤት

1. የቀበሌ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት የመስተዳደር ምክር ቤት ጭምር ሆኖ ያገለግላል።
2. የቀበሌ ምክር ቤት የራሱ ጽሕፈት ቤት እስከሚኖረው የቀበሌ አስተዳደሩን ጽሕፈት ቤትና የቢሮ መገልገያዎች በመጋራት ይሠራል።

## አንቀፅ 99
## የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

1. የቀበሌው ማህበራዊ ፍርድ ቤት በዚህ ሕገ መንግስት የቀበሌው ማህበራዊ የዳኝነት አካል ሆኖ ተቋቁሟል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሠናል።
2. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በዚህ ሕገ መንግስት አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 4 ስር በተደነገገው መሠረት ተመርጠው የሚሾሙ ይሆናሉ።
3. የማህበራዊ ፍርድ ቤት የስራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የስራ ዘመን ነው።

# ምዕራፍ አስር
## የክልሉ ፖሊሲ አላማዎች

## አንቀፅ 100
## አላማዎች

1. ማንኛዉም የመንግስት አካል የፌዴራሉንና የክልሉን ህግ መንግስት ሌሎች ህጎችና ፖሊሲዎችን በስራ ላይ ሲያዉል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት አላማዎች እና መርሆዎች ላይ መመስረት አለበት።
2. በዚህ ምዕራፍ "መንግስት" ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ይሆናል

## አንቀፅ 101
## ፖለቲካ ነክ አላማዎች

1. መንግስት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት የአፋር ክልል ህዝብ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።
2. መንግስት የብሔረሰቦችና የህዝቦች ማንነት የማክበር በዚህ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸዉ እኩልነትን አንድነትን ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 102
## ኢኮኖሚ ነክ አላማዎች

1. መንግስት ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች በክልሉ በተጠራቀመ ዕዉቀትና ሀብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ሀላፊነት አለበት።
2. የክልሉ ኢኮኖሚ በዋነኛነት የተመሠረተው በእንስሳት ሀብት በመሆኑ መንግሥት ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ሲቀርፅ የአርብቶ አደሩን የኑሮ መሠረት በማሻሻል ወደ ተረጋጋ ኑሮ የሚመጣበትንና የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሃላፊነት አለበት።
3. መንግስት የክልሉ ነዋሪዎችን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል ዕኩል እድገት እንዲኖራቸዉ ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት።
4. መንግስት የተፈጥሮና የሠው ሠራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋዉ ሲደርስም ለተጎጂዉ እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ አለበት።
5. መንግስት የክልሉን ኢኮኖሚ ከሀገር አቀፍ ኢኮኖሚ ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ከፌዴራል መንግስት አካላት ጋር ጥረት ያደርጋል።
6. መንግስት የግል ባለሀብቶችን በክልሉ ልማት እንዲሳተፍ ያበረታታል፤ አስፈላጊውንም እገዛ ያደርጋል።
7. መንግስት መሬትንና ተፈጥሮ ሀብትን በህዝብ ስም በይዞታዉ ስር በማድረግ ለህዝቡ የጋራ ጥቅምና ዕድገት እንዲዉሉ የማድረግ ሀላፊነት አለበት።
8. መንግስት የክልሉ የልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት ህዝቡን በየደረጃዉ ማሣተፍ አለበት የህዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት።
9. መንግስት የህዝቡን ዕዉቀት ጉልበትና ገንዘብ በማቀናጀት ፈጣን ልማት የሚረጋገጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት። ህዝቡ በክልሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረዉ ማድረግ አለበት ስለሆነም ህዘቡ ዕቅዶችና ፖሊሲዎችን ለመደገፍ ብቻ ሳይሆን በማስፈፀምና በመገምገም መሳተፍ አለበት።
10. መንግስት በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የሚሣተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።
11. መንግስት የሠራተኛዉን ህዝብ ጤንነት ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 103
## ማህበራዊ አላማዎች

1. የአገሪቱና የክልሉ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የክልሉ ነዎሪዎች የትምህርት የጤና አገልግሎት የንፁህ ዉሃ የመኖሪያ የምግብና ማህበራዊ ዋስትና እንደ፩ደራጅ ያደርጋል።
2. ትምህርት በማናቸዉም ረገድ ከሀይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶች፣ ከባህላዊ ተፅዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ ይካሔዳል።

## አንቀፅ 104
## ባህል ነክ አላማዎች

1. የክልሉ መንግስት መሠረታዊ መብቶችንና ሠብአዊ ክብርን ዲሞክራሲንና ህገ መንግስቱን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጐለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።
2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የያንጉደራሳና የአዋሽ ፓርኮችን የፌዴራሉ መንግስት ከሚያደርገው ጥበቃ በተጨማሪ የክልሉ መንግስትና ህዝብ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው።
3. የክልሉ መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን ስይንስንና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት።
4. መንግስት ወጣቱን ትውልድ የመንከባከብ በተሟላ ሥነ ምግባር የማነፅ፣ ከሱስ ነፃ የሆነና፣ በአካልም ሆነ በአዕምሮ ጠንክሮ ኃላፊነትን የሚሸከም፣ አገሩን የሚወድ እና ለወገኑ የሚቆረቆር ብቁና በራሱ የሚተማመን ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት አለበት።
5. የክልሉ የሥራ ቋንቋ ለሆነው የአፋርኛ ቋንቋ ዕድገተ መንግስት ልዩ ትኩረት በመስጠት ይንቀሳቀሳል።
6. የክልሉ መንግስትና ህዝብ በክልሉ ውስጥ የገኙትን የአርኪኦሎጂ ግኝቶችና የታሪክ ቅርሶችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀፅ 105
## የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ አላማዎች

1. መንግስት ሁሉም የክልሉ ነዋሪ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረዉ የመጣር ኃላፊነት አለበት።
2. ማንኛዉም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢዉን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት።
3. የህዝብን የአካባቢ ደህንነት በሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ስራ ላይ በሚዉልበት ጊዜ የሚመለከተዉ ህዝብ ሁሉ ሃሣቡን እንዲገልፅ ማድረግ አለበት።

www.abyssinialaw.com

4. መንግስትና የክልሉ ነዋሪዎች አካባቢያቸዉን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸዉ። በተለይ በረሃማነትን ለመከላከልና ለመግታት መንግስትና ህዝብ አስፈላጊዉን ሁሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## ምዕራፍ አስራ አንድ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ 106
### የአስቸካይ ጊዜ አዋጅ

1. በፌዴራሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 93 ንዑስ አንቀፅ አንድ(1) (ሀ) እና (ለ) እና በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ(47) አርባሰባት ንዑስ አንቀፅ(2) ሁለት(ወ) በተደነገገዉ መሠረት ማናቸዉም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ባልሆነበት ጊዜ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ ሀምሳ ስምንት (58) ንኡስ አንቀፅ (7) በተሠጠዉ ስልጣን መሠረት ያስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አዉጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል።
2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአስቸካይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌዉን አዉጥቶ በስራ ላይ ባዋለ በአስራ አምስት ቀን ዉስጥ አፈ ጉባኤዉ የክልሉን ምክር ቤት አስቸካይ ስብሰባ እንዲጠራ ማሳወቅና የአስቸካይ ጊዜ ድንጋጌዉን ለምክር ቤቱ በማቅረብ ማፀደቅ አለበት።
3. የክልሉ መስተዳድር ያወጣዉ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በክልሉ ምክር ቤት ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለዉ ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሦሥተኛ ደምፅ ሲወሰን የአስቸ[illegible]ይ ጊዜ ድንጋጌዉን በየአራት ወሩ እንዲታደስ ለማድረግ ይችላል። ይህን በስራ ላይ ማዋል የሚችለዉ ግን ለሶስት ጊዜ ብቻ ነዉ።
4. የክልል መስተዳድር ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ የሚያወጣቸዉ ደንቦችና የሚወስዳቸዉን እርምጃዎች በማናቸዉም ረገድ በዚህ ህገ መንግስት አንቀፅ 15 አንቀፅ 16 አንቀፅ 18 (1) እና (2) ፣ 21 (1) ፣ 24 (1) ፣ 27 (1) እና 39 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም።

www.abyssinialaw.com

## አንቀፅ 107
## የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ

1. የክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና ከህግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሶስት የቦርዱ አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ መርማሪ ቦርድ ማቋቋም ይችላል። ቦርዱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በክልል ምክር ቤት በሚፀድቅበት ጊዜ ይቋቋማል።
2. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ሀላፊነቶች ይኖሩታል።
   ሀ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ምክንያት የታሠሩትን ግለሠቦች በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ይፋ ማድረግና የተሠሩበትን ምክንያት መግለፅ።
   ለ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ወቅት የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸዉም ረገድ ኢሰብአዊ አለመሆናቸዉን መቆጣጠርና መከታተል
   ሐ. በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እርምጃዎች ኢሠብአዊ ድርጊት የፈፀሙትን ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ
   መ. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ እንዲቀጥል ለክልሉ ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለዉን አስተያየት ለምክር ቤቱ ማቅረብ ።

## አንቀፅ 108
## የክልሉ ዋና ኦዲተር

1. የክልሉ ዋና ኦዲተር በርዕስ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማል።
2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉ መንግስት ተቋማትና የሌሎች መስሪያ ቤቶችን ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልል ምክር ቤት የተመደበዉ አመታዊ በጀት በበጀት አመቱ ዉስጥ እንዲሠሩ ለተወሠኑት ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።
3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመስሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል
4. የዋና ኦዲተር ተጠሪነት ለክልል ምክር ቤት ይሆናል።
5. የዋና ኦዲተር ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል።

## አንቀፅ 109
## የህገ መንግስት ማሻሻያ ሀሳብ ስለማመንጨት

የዚህ ህገ መንግስት ማሻሻያ ሀሳብ አጀንዳ ሆኖ ለዉይይት የሚቀርበዉ

ሀ. በክልሉ ምክር ቤት አባላት አንድ ሶስተኛ ጥያቄ ወይም

ለ. በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአብላጫ ድምፅ ዉሣኔ ወይም

www.abyssinialaw.com

ሐ. በክልሉ ዉስጥ ካሉ የወረዳ ምክር ቤቶች በአንድ ሶስተኛዉ ጥያቄ ወይም

መ. በክልሉ ዉስጥ ካሉ የቀበሌ ምክር ቤቶች በአንድ ሶስተኛዉ የተጠየቀ ከሆነ ለዉይይትና ለዉሣኔ የህገ መንግስቱ መሻሻል ለሚመለከታቸዉ ክፍሎች ይቀርባል።

## አንቀፅ 110
## የህገመንግስት ማሻሻል

1. የዚህ ህገ መንግስት ምዕራፍ ሁለትና ሶስት የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚሻሻሉት በፌዴራል ህገ መንግስት አንቀፅ 105 መሠረት በማድረግ ይሆናል::
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ከተዘረዘሩት ዉጭ ያሉት የህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለዉ አካሄን ብቻ ይሆናል::
   ሀ. በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የወረዳ ምክር ቤቶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በአብላጫ ድምፅ ሲያፀድቁት።
   ለ. በክልሉ ምክር ቤት አባላት በሶስት አራተኛ ድምፅ ሲያፀድቁት ነዉ::
3. የዚህ ንዑስ አንቀፅና የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ሁለት ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት የቀረበዉን ማሻሻያ።
   ሀ. በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙ ወረዳ ምክር ቤቶች ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ብልጫ ሲያፀድቁትና።
   ለ. የክልሉ ምክር ቤት በሶስት አራተኛ ድምፅ ሲያፀደቁት ነዉ::

## አንቀፅ 111
## የመጨረሻ ህጋዊ ኮፒ

የዚህ ህገ መንግስት የአፋርኛ ቅጅ የመጨረሻው ህጋዊ ዕውቅና ያለው ሠነድ ነው::